# የመንግሥት ወንጌል!

Tip:
የመጨረሻው ዘመን የሕይወት መጠይቆች/ የአገልግሎት መስፈርቶች / ፦
1. በአላማ እውቀት ላይ የተመሰረተ!
2. ማንነትን / ባሕሪይን / አመለካከትን በመገንባት ላይ ያተኮረ!
3. ብቃትን / ችሎታን / ስጦታን የመግለጥ!

ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ **የመንግሥትንም ወንጌል** እየሰበከ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር። (ማቴ 4፡23)

እርሱ ግን። ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎቹ ከተማዎች ደግሞ **የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል** እሰብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው።(ሉቃ 4፡43)

ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ **የመንግሥት ወንጌል** በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል። (ማቴ 24፡14)

የመጀመሪያው ወንጌል የትኩረት ማእከል "የእ/ር መንግሥት" ነበር!
⇒ የመጥምቁ ዩሐንስ ዋና መልእክት ይኸው ነበር (ማቴ 3፡1…)
⇒ የኢየሱስም ከአገልግሎቱ ጅማሬ እስከ እስካረገበት ቀን ድረስ ያስተማረው ይህንኑ ነበር (ማቴ 4፡17… ሐዋ 1፡3)
⇒ ጳውሎስ ዘመኑን ሁሉ የሰበከው ነገር ቢኖር ስለ እ/ር መንግሥት ነው (ሐዋ 20፡25፤ ሐዋ 28፡23፣31)
⇒ ሐዋሪያትም ይህንኑ ሰበኩ (ሐዋ 8፡12)

<u>የእ/ር መንግሥት ማለት ምን ማለት ነው?</u>

- መንግሥተ-ሰማይ፦ ያለተቀናቃኝ ብቻውን የሚገዛ እ/ራዊ (theocratic) አስተዳደር የሰፈነበትን መንፈሳዊ ስፍራ (realm) ወይንም ክልል ሲሆን
- የእ/ር መንግሥት፦ የዚህ ሰማያዊ መንግሥት አስተዳደራዊ ሥርዓት ነው።

ከእ/ር መንግሥት አይነተኛ ባሕሪያት ጥቂቱ እነሆ፦

- በኃይል የምትመጣ (ማቴ 12፡28፤ 1ቆሮ 4፡20) በመርህ ት/ትና በጥበብ ምክር ቀስ በቀስ የምትሰፋ መሆኗ (ማቴ 13፡33)
- በዳግመኛ መወለድ (በፍጹም የማንነት ለውጥ) ብቻ የሚገባባት (ዩሐ 3፡3) በኃይል የምትወረስ (ማቴ 11፡12)
- የምትመጣው በሰዎች ላይ ነው (ሉቃ 17፡21) - ይኸውም የእ/ርን ልጆች ወደ ተጽእኖና የመግዛት ስፍራቸው ለመመለስ ነው!
- በሙላት የምትገለጠው ሰዎች ሁሉ በእ/ር ቃል አመለካከታቸው ተለውጦ በመንግሥቱ ስርዓት ሲሞሉ - ይኸውም ሁሉ በክርስቶስ ሲጠቀለል ነው! (ማቴ 13፡31-32፤ ኤፌ 1፡9)

## <u>የመንግሥት ወንጌል</u>

- መንግሥት = አገዛዝን፣ አስተዳደርን፣ ሥልጣንን፣ ሃይልን ያሳያል
- ወንጌል = የምስራች፣ መልካም ዜና ማለት ነው

⇒ ስለዚህ የመንግሥት ወንጌል ስለ አገዛዝ፣ አስተዳደር ወይንም ሥልጣን የሆነ የምስራች ነው። ይህም፦

- ስለ እ/ር አገዛዝ.. ወደ ሰው መመለስ ነው!
- ሰው አጥቶ ወደነበረው የግዛት ስፍራው ስለመመለሱ ነው!

መንግሥትም ግዛትም ከሰማይም ሁሉ በታች ያሉ የመንግሥታት ታላቅነት ለልዑሉ ቅዱሳን ሕዝብ ይሰጣል፤ መንግሥቱ የዘላለም መንግሥት ነው፥ ግዛቶችም ሁሉ ይገዙለታል ይታዘዙለትማል። (ዳን 7፡27)

⇒ የመንግሥቱ ወንጌል ከሲኦል የማምለጥ ነጠላ ዜና ሳይሆን ለሰዎች ሁሉ **ወደዘፍጥረት አንድ በመመለስ** (ዘፍ 1፡26-28) የሚሰጥ የብዙ ሰማያዊ ችሮታዎች ጥቅል ነው። ይህም፦

- በሚመጣው ዓለም የዘላለም ሕይወትን
- በአሁኑም ዘመን ደግሞ ብዙ በረከትን የያዘ ነው!! (ሉቃ 18፡30)

(የሃጢያት ስርየት አልፎም የጽድቅ ሕይወት.. ከበሽታም መፈወስ አልፎም በጤንነት መኖር..)

## <u>የመንግሥቱ ወንጌል አላማ፦</u>

1. ሰው የተፈጠረበት አላማ  በእ/ር መልክና ምሳሌ ማንነት ሆኖ ምድርን ማስተዳደር ወይንም መግዛት ነበር - ይህም በሰማይ ያለውን የእ/ር መንግሥት በኃላፊነት በምድር እንዲቀጥል ማድረግ ነበር!
2. ስለዚህ የሰው ውድቀት የመንግሥት ውድቀት ሆነ! በሌላ አባባል ሰውም ሆነ የሰማዩ መንግሥት ሥርዓት በሰዎች መካከል የነበረውን የማስተዳደር ስፍራ አጣ!
3. የወንጌሉ ግንባር ቀደም አላማም የጠፋውን ማስመለስ ነው! የጠፋው መንግሥት ነው!
4. የእ/ር ፈቃድ መፈፀም የሚሆነውም መንግሥቱ በምድር ላይ ስትመሰረት ነው!
5. የሰው መዳን ያስፈለገውም የእ/ርን መንግሥት አስተዳደር ወደ ተጽእኖ ስፍራው ለመመለስ ነው!

በአንጻሩ ግን ከታሪክ እንደምንረዳው የመንግሥቱ ወንጌል ከጊዜ ወደ ጊዜ የመጀመሪያ መልእክት አትኩሮውን እየለቀቀና ይዘቱን እያጠበበ አሁን ባለንበት ሁኔታ፦

- ምድርን መሪ አልባ ፕላኔት እንድትሆን
- ቤ/ክንን መንግሥታዊ ሳይሆን ሃይማኖታዊ ተቋም ብቻ እንድትሆን
- ኢየሱስም እንደብዙዎች የሰማይ መንግሥት መምጣት መልእክተኛና ንጉሥ ሳይሆን የአንድ ሃይማኖት መሪ መስሎ እንዲታይ
- የመንግሥቱን ቃልና ለዚህ አለም ኑሮ የማይጠቅም (irrelevant) እንዲሆን/ መስሎ እንዲታይ አድርጎታል

## ተሃድሶ ያስፈልገናል!!!

<u>በእርግጥ በዚህ ዘመን እየሰበክን ያለነው የመንግሥቱን ወንጌል ነውን?</u>

ከመንግሥቱ ወንጌል አይነተኛ ባሕሪያት ዋንኞቹ፦

- *በሃይልና በሥልጣን የተሞላና እንዲሁም የሚታወጅ መሆኑ!*
  (በሰዎች አስተያየት / ሌሎች በሚያወጡት ቅድመ ሁኔታ/ የሚወሰን ሳይሆን በደራሲው በእ/ር ፈቃድ ብቻ የሚሰበክ መሆኑ) (ማር 1፡22፤ ሐዋ 5፡29)
- *ሰዎችን ወደተፈጠሩበት አላማ /ኃላፊነት/ የሚያመላክት መሆኑ!*
  (በማምለጥና በሽሽት መንፈስ /በመነጠቅም ሆነ በሌላ መንገድ/ ተይዘው ለኃላፊነትን ከማይበቁበት ሕይወት የሚጠብቅ - ኃላፊነትን የሚያስተምር)
- *ሰውን ወደ ገዢ /አስተዳዳሪ/ ማንነቱ የመመለስ ብቃት ያለው መሆኑ!*
  (በበርካታ የኑሮ ጥያቄ ተይዘው ለራሳቸው እንኳ ከማይበቁበት የሕይወት ክልል በማውጣት ተጽእኖ ለማድረግ የሚያዘጋጅ መሆኑ)
- *የአዲሱን ሰው ብቃት የሚያጎላ መሆኑ!*
  (አለመብቃትንንና አለመቻልንና ጉድቶችን ብቻ በማግዘፍ የተሸናፊነትን አመለካከትን የማይገነባ)
- *በሚመጣው አለም ብቻ ሳይሆን በዚህ አለም ያለውንም አስፈላጊነት (relevance) እና ትርፍ ማሳየት የሚችል!*
  (ግማሽ ያልሆነ ወንጌል!)
- *በጠንካራ የመርህ ት/ቱና በሚሰጠው ጥበብና ማስተዋል ተጽእኖው እየሰፋ የሚሄድ መሆኑ!*
  (እንጂ የሰዎችን ጊዜአዊ ሕመም በሚነካካ ወይንም ስሜትን በሚኮርኩር አገልግሎት ጥበብ ያለ የማይመስለው)
- *የገዢውን /የጌታን የእ/ርን / ቃል ቢገባም ባይገባም በንጹህነቱ /በራሱ ወግ/ የሚያውጅ!*
  (እንጂ በግል ልምምድ መነጽር የማያይ ወይንም ከልምዶች፣ ባህሎችና የተለመዱ አሰራሮች ጋር ለማስማማት የማይሞክር!)

## ወደ መንግሥቱ ወንጌል እንመለስ!!!

ለጥያቄዎ:- Contact alazar_1@yahoo.com